ጠቃሚ ሀቆች ያዘለ ወረቀት (ፋክት ሺት)

በጉርሻ (ቲፕ) ደመወዝ ለሚያገኙ ሠራተኞች ፍትሃዊነት የማሻሻያ ሕግ (ፐይድ ዌጅ ዎርከርስ ፈየርነስ አመንድመንት አክት)

የሰብአዊ መብቶች ቢሮ

የተሻሻለበት ቀን፦ ሰፕቴምበር 14፣ 2026

ጉርሻ (ቲፕ) ያገኛሉ? መብቶች አሉዎት! በዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ ያሉዎትን መብቶች ይወቁ

ጉርሻ (ቲፕ) እንደ ደመወዝ ለሚያገኙ ሠራተኞች የተሰጡ መብቶች እና ጥቅማጥቅሞች

ጉርሻ (ቲፕ) ለሚያገኙ ሠራተኞች ፍትሃዊነት የማሻሻያ ሕግ (ፐይድ ዌጅ ዎርከርስ ፈየርነስ አመንድመንት አክት - TWWF)፣ ቲፕ እንደ ደመወዝ የሚያገኙ ግለሰቦችን የሚቀጥሩ የዲስትሪክቱ አሰሪዎች ለሠራተኞቻቸው ስለ መብቶቻቸው እና ጥቅማጥቅሞቻቸው እንዲያሳውቁ ያስገድዳል። እነዚህን መብቶች ከሚሰጡት ሕጎች መካከል አንዳንዶቹ በዲስ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ስራ ላይ የሚዉሉ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ በሥራ አገልግሎቶች መምሪያ (DOES) በኩል ተፈጻሚ ይሆናሉ።

በዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) በሚያስፈጸሚቸው ሕጎች ሥር ያሉ የሠራተኛ መብቶች

- በዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ሥር ከለላ በተደረገላቸው መገለጫዎች ላይ ተመስርቶ በሥራ ቦታ ከሚደርስ አድልዎ ነፃ የመሆን፤
- የጾታ ትንኮሳን ጨምሮ በሥራ ቦታ ከሚደርስ ማንኛውም ትንኮሳ ነፃ የመሆን፤
- ብቁ እና መስፈርቱን የሚያሟሉ ከሆኑ፣ እንዲሁም ደግሞ 20 ወይም ከዚያ በላይ ሠራተኞች ባሉትና ሕጉ የሚመለከተው አሰሪ ዘንድ የሚሰሩ ከሆነ፣ ክፍያ ሳያገኙ የቤተሰብ እና የሕክምና ፈቃድ የመጠየቅ እና የመጠቀም፤
- የልጅዎን ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ስራዎች ለመሳተፍ የፈቃድ ጊዜ የመጠየቅ፤
- ለሃይማኖታዊ ምክንያቶች፣ ለአካል ጉዳት፣ ወይም ከእርግዝና ጋር ለተያያዙ የጤና ሁኔታዎች በሥራ ቦታ ተገቢውን ማመቻቸት የማግኘት፤
- በአጠቃላይ እየተከፈልዎት እረፍት የሚያገኙበት ሕግ (ዩኒቨርሳል ፐይድ ሊቭ አክት) ሥር ከሚደርስ ጣልቃ ገብነት እና የበቀል እርምጃ ነፃ የመሆን፤
- ከእነዚህ መብቶች መካከል ስለ ማናቸውም በመወያየትዎ ወይም ተግባራዊ በማድረግዎ ምክንያት ከአሰሪ ከሚወሰድ የበቀል እርምጃ ነፃ የመሆን፤ እና
- በሥራ ቦታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሲያጋጥም ለሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) አቤቱታ የማቅረብ።
- ከእነዚህ መብቶች ጋር የተያያዙ ችግሮች ካጋጠሙዎት፣ ለሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) አቤቱታ ያቅርቡ።

የሥራ ስምሪት አገልግሎቶች መምሪያ (DOES) በሚያስፈጸሚቸው ሕጎች ሥር የደመወዝና የሥራ ሰዓት መብቶችም አለዎት

- ቢያንስ ዝቅተኛውን የደመወዝ ወለል የማግኘት፤
- ክፍያን በወቅቱ የማግኘት፤
- ዝርዝር መረጃ የያዘ የክፍያ ሰነድ (ፐይ ስታብ) የመቀበል፤
- እየተከፈልዎት የሕመም እና የደህንነት ፈቃድ (ፐይድ ሲክ ኤንድ ሴፍ ሊቭ) የማጠራቀም እና የመጠቀም፤

- በአጠቃላይ እየተከፈልዎት እረፍት የሚያገኙበት ሕግ ሥር ለተወሰኑ ብቁ ለሚያደርጉ ሁነቶች እየተከፈልዎት ፈቃድ ማግኘት የመቻል፤
- ከሥራ ጋር ለተያያዘ ሕመም ወይም ጉዳት ካሳ የማግኘት፤ እና
- በሥራ ቦታ የደመወዝ ክፍያ ጥሰት ሲከሰት ለሥራ ስምሪት አገልግሎቶች መምሪያ (DOES) አቤቱታ የማቅረብ።

ከእነዚህ መብቶች ጋር የተያያዙ ችግሮች ካጋጠሙዎት፣ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶች መምሪያ (DOES) የደመወዝ እና የሥራ ሰዓት ቢሮን (ኦፊስ ኦፍ ዌጅ-አወር) በስልክ ቁጥር (202) 671-1880 ያነጋግሩ ወይም does.dc.gov ድረ-ገጽን ይጎብኙ።

የአሰሪ የማስታወቂያ እና የመለጠፍ ግዴታዎች

አሰሪዎች እነዚህን ማስታወቂያዎች ሁሉም ሠራተኞች ሊያዩዋቸው በሚችሉበት እና ተደራሽ በሆነ ቦታ (ለምሳሌ እንደ የሠራተኞች ማረፊያ ክፍል በመሳሰሉ ቦታዎች) መለጠፍ እና መከታተል አለባቸው። እንዲሁም የጾታ ትንኮሳ አቤቱታን ለዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል ጨምሮ፣ የጾታ ትንኮሳ መከላከያ ፖሊሲያቸውን ለሁሉም ሠራተኞች ማሰራጨት አለባቸው።

የጥሰት አቤቱታን ለሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል

በግሉ ዘርፍ ያለ አሰሪ፣ የጾታ ትንኮሳ አቤቱታን ጨምሮ ከእነዚህ መብቶች እና ጥቅማጥቅሞች መካከል ማናቸውንም ያላግባብ እንደነፈገዎት ወይም እንደጣሰ ካመኑ፣ ድርጊቱ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ባለው በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ለዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፤ በቀኝ በኩል ያለውን የኪውአር (QR) ኮድ ስካን በማድረግ የመግቢያ መጠይቁን ይሙሉ፣ ወይም ድረ-ገጻችንን በመጎብኘት በ https://ohr.dc.gov/service/file-discrimination-complaint በኩል ለሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ያስገቡ።

ስለ ሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) የሥራ ሂደት ጥያቄዎች ካሉዎት በስልክ ቁጥር (202) 727-4559 በመደወል ምላሽ ማግኘት ይችላሉ።

ስለ ሥራ አገልግሎቶች መምሪያ (DOES) የሥራ ሂደት የተመለከቱ ጥያቄዎች ካሉዎት በስልክ ቁጥር (202) 671-1880 በመደወል ምላሽ ማግኘት ይችላሉ።

የጾታ ትንኮሳ መከላከያ ፕሮግራምን (ሴክሸዋል ሀራስመንት ፕረቨንሽን ፕሮግራም) በተመለከተ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በ tipsdc@dc.gov ኢሜይል ያድርጉልን።

የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ውሳኔ ስለሚሰጥባቸው የአቤቱታ ዓይነቶች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በ OHR@dc.gov ኢሜይል ያድርጉልን።